የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር ፌ2ም/ሕፌ/5/313
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

<u>መቀሌ</u>

ለሃለቃ ተአረ ደስታ ወኪል ወ/ሮ ጥበቡ ተአረ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 62 ንኡስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 83 ንኡስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሕገ መንግስታዊ ክርክሮችን አይቶ ሕገ መንግስቱን በመተርጐም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ምክር ቤቱን ለማጠናከርና ስልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 56 መሰረት ምክር ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ አጠቃላይ ውጤት እንደሚኖረው እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖችም ውሳኔውን የማክበርና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ሃለቃ ተአረ ደስታ ባቀረቡት ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተመልክቶ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ 4/አራት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የተላከላችሁ ስለሆነ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም አስታውቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ከሪያ ኢብራሂም አሊ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ

<u>ግልባጭ</u>

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
  <u>በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት</u>